# የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች እና ኢሕአዴግ፤ <u>ከዚኽ ወዴት?</u>

*ከአያል ሰው ደሴ፤- የግል አስተያየት*

***<u>ክፍል ሦስት</u>*** *<u>( ከክፍል ሁለት የቀጠለ )</u>*

## <u>ሐ) አገር-ወዳድና ሕዝባዊ (ዴሞክራሲያዊ) ኃይሎች፤</u>

ከፍ ሲል በ'ለ' ሥር ለማሣየት እንደተሞከረው ለአገራችንና ለሕዝቧ አዎንታዊ ለውጥን ለማስገኘት በልዩ ልዩ መልክ የሚታገለውና በጥቅሉ "ተቃዋሚ ክፍል" የተባለው ወገን ሥልጣን ላይ ካለው ገዥ ክፍል ከኢሕአዴግ ጋር የሚኖረውን አንፃራዊ አሠላለፍ በተገቢ መመርመር ያስፈልጋል።

ትግሉ ጣምራ መሆኑ ግልፅ ነው። በአንድ በኩል መሠረታዊና እንደ ልዕለ-ግብ የሚቆጠረው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ፍትኀን፣ እኩልነትንና አስተማማኝ አንድነትን የሚያጎናጥፍ ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአገሪቱ እውን እንዲሆን የሚደረግ ትግል ሲሆን፤ በሌላ በኩል ወደዚኽ ልዕለ-ግብ ለመድረስ የሚደረገውን ጥረት ከሚገረግሩና እንቅፋት ከሆኑ ኃይሎች ጋር የሚደረግ ፍልሚያ ይሆናል። ይኽ ሁለተኛው የቅርብ-ጊዜ-ግብ ሊባል ይችላል። ለአዎንታዊ ለውጥ የቆመው ክፍል ወደ ልዕለ-ግቡ ለመገስገስ ከማሰቡ በፊት የቅርብ-ጊዜ-ግቡን መጨበጥ ይኖርበታል። ይኸን የቅርብ-ጊዜ-ግብ ለመጨበት የሚደረገው ጥረት ግን ልዕለ-ግቡ ላይ ያለውን ንጥጥር በዋናነት የያዘና ያልለቀቀ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበትና ምን ጊዜም ገዥነት ሊኖረው እንደሚገባ ያጤኗል። የቅርብ ጊዜው ግብ በተገቢና በብቃት እንዲሰምር ከተደረገ በማያሻማና ግልፅ በሆነ መንገድ ገዥው ፓርቲ ሕወሓት/ኢሕአዴግ በአንድ መልኩ ወይም በሌላ የልዕለ-ግቡ አካል እንዲሆንም ሆነ አሉታዊ ሚና እንዲኖረው በማድረጉ በኩል ወሳኝ ይሆናል።

ወደዚኽ የቅርብ-ጊዜ-ግብ የሚደረገው ትግል እንዲሣካ ሊወገድ/ዱ (ሊቸነፍ/ፉ) የሚገባውን/የሚገባቸውን ክፍል/ክፍሎች ድርጅታዊ ተፈጥሮ፣ መሠረታዊ ፍልሥፍና፣ ተቋምና ይዞታ ጠንቅቆ ማወቅና ይኸን/እነዚኸን ለመቋቋምና ለማቸነፍ የሚያስችል መጣኝ አደረጃጀትና አሠላለፍ መያዝ ያስፈልጋል። ምንም ከመደረጉ በፊት ለዕለ-ግቡ መሣካት ቅድሚያ እንቅፋት የሆነውን/የሆኑትን ተፃራሪ ክፍል/ክፍሎች ይዞታ፣ ዓላማና አጠቃላይ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ማወቁ መጣኝ አደረጃጀትና አሠላለፍ ለመያዝም ሆነ ብቁ የትግል ትልም ለመንደፍና ለመከተል ቁልፍ ስለሚሆን ይኽ የቅርብ-ጊዜ-ግቡን ውጤት በመሳካቱም ይሁን ባለመሳካቱ ላይ ወሳኝነት አለው። በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት እንዲሰፍን የሚደረገው ትግል ላይ በዋና እንቅፋትነት ከቆሙት ኃይሎች ውስጥ ኢሕአዴግ በተቀዳሚነት ስለሚፈረጅ እንግዲኽ ለለውጥ የቆመው አገር-ወዳድና ሕዝባዊ (ዴሞክራት) ወገን ይኸንን ኃይል አስገድዶ እርባናና ትርጉም ወዳለው ድርድር እንዲመጣና የልዕለ-ግቡ አካል እንዲሆን ማድረግ ወይም ጨርሶ እንዲንበረከክ ለማድረግ የዚኽን ኃይል (የኢሕአዴግን) ማንነትና ምንንነት ከያዘው መሠረታዊ የፖለቲካ ፍልሥፍናና አደረጃጀት አኳያ ወሳኝነት ያለው አደረጃጀትንና አሠላለፍን መያዝ እና መጣኝ የትግል ስልትና የግብ ትልም (ስትራቴጂ) መከተልን የግድ ይላል ማለት ነው።

ስለዚኽ ለአዎንታዊ ለውጥ የቆመው አገር-ወዳድና ሕዝባዊ (ዴሞክራት) ወገን እስካሁን የተከተላቸው የአደረጃጀትና የአሠላለፍ መሥመሮችን ዞር ብለን በአጭር-በአጭሩ የምንቃኘው የወደፊቱን አካሄድ ለመተለም ካለፉት ተመክሮዎች ትምሕርት መቅሰሙ ስህተቶችን ላለመድገምና በጎ ጎኖችን ለማዳበር ጠቃሚ ስለሚሆን ነው።

በአገራችን ለውጥ እንዲመጣ በተደራጀ መልክ ከተደረጉ ትግሎች ውስጥ ደርግን ለማስወገድ በነበረው ትግልና ከዚያም ሕወሓት/ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ አንስቶ ከተደረገው ፍልሚያ ብዙ ልምዶች እንዳሉ ግልፅ ቢሆንም ምን ያኽል አዎንታዊነት ያለው ትምሕርት መቅሰም እንደተቻለ ግን በእርግጠኝነት መናገር ያስቸግር ይሆናል፣ ምናልባትም አከራካሪ ሊሆን ይችላል። በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው ግን በአሁኑ ጊዜ ከኢሕአዴግ አንፃር ከቆመው የለውጥ ኃይል የበለጠ (አቅሙም ሆነ ሁኔታው የተሻለ ስለሆነለት ሊሆን ይችላል) ገዥው ክፍል ከሂደቱ ብዙ የተማረ መሆኑን ነው።

*ደርግን በማስወገዱ ትግል ሕወሓት የነበረው ሚና ግልፅ ቢሆንም ያ አስተዋፅዖ መሠረታዊ ጎጠኛ አቋሙን የሚያካክስ ይመስል ድርጅቱ ሥልጣን የመያዝ ዕድል ሲገጥመው ሲሆን እምነቱንና ድርጅታዊ ማንነቱን መቀየርና ሃቀኛ አገራዊ እርቅና ሰላም ሂደትን በመከተል የአገራችንን መሠረታዊ ችግሮች በአስተማማኝና ዘለቄታዊነት ባለው መልክ እንዲፈቱ ማመቻቸት፣ ቢያንስ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለፈጠረለት መሰል-የሌለው ጥሩ አጋጣሚ አክብሮ ማመስገን ሲገባው ጋፍኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለድርጅቱ ውለታ እንዳለበት አድርጎ በመቁጠር የፈለገውን ማድረግን እንደ አንጡራ መብት መቁጠሩ የዞረበት ስሊት ቢሆንም በመሪዎቹ ዘንድ እንደ መደበኛና ጤነኛ አመለካከት ሆኖ የሚታይ መሆኑ ከሚያደርጓቸው ሕዝብን የናቁ አምባ-ገነን ቀጣይ ተግባራት መረዳት ይቻላል:: ከድርጅቱ ተፈጥሮ ባኅሪና ፍልሥፍና አንፃር ሲታይ ግን የድርጅቱ መሪዎች እስከ-አሁን ያደረጉትም ይሁን ወደ-ፊት የሚያደርጉት ሕዝብን ቁጥር ውስጥ ያላስገባ ውሳኔና እርምጃ ሊሆን የሚችል ብቻ ሣይሆን የሚጠበቅ መሆን ይኖርበታል::*

*ምን ጊዜም ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘለቄታዊ የጋራ ጥቅሙን ለማስከበርና ለጋራ ኅልውናው መረጋገጥ የተሻለ ምርጫ የሚሆነው ሁሉንም ዜጎች በእኩል ዓይን ማየት የሚሣነው ፖለቲካዊ ብሔረሰበኛ (የጎሣ ፖለቲካ) ከሚያስከትለው መዘዝና ጥንውት ተላቆ፣ ሕዝብ የሥልጣን ብቸኛ ምንጭ እንደመሆኑ የሥልጣኑ ባለቤት የሚሆንበትና አድልዖ የሌለበት፣ ዜጎች እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑበትና ሁለንተናዊ መብቶቻቸው የሚከበሩበት የሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤት መሆን ሲቻል ብቻ ነው:: ይኸ ደግሞ እውን እንዲሆን ተጠያቂነትና ኃላፊነት ያለበት፣ በሕዝብ ፈቃድና ይሁንታ ብቻና በሕዝብ ልዩነት ላይ ሣይሆን በሕዝብ አንድነት ላይ የቆመ መንግሥት መኖርን ይጠይቃል:: ለዚኸ የጋራ ጥቅም-አስከባሪ ግብ የሚደረገው ሕዝባዊ የመብትና የአንድነት ትግል ፍሬ የሚሰጠው ግን ሁሉም የሚቀበለውና ቀደም ሲል ከተደረጉ ጥረቶች ጠቃሚ ልምዶችን ቀስሞ አዳዲስ ክስተቶችን ባስተባቃ መልክና ሁኔታው በሚጠይቀው መጠን በአዲስ ቅኝትና መንፈስ በቁርጠኝነት መካሄድ ሲችል ነው::*

*ሁሉንም ዜጎች የነኩ ችግሮችን ለመፍታት በሚል ይሁን በሌላ ምክንያት የአንድን አገር ሕዝብ በብሔረሰብ (በጎሣ) በመከፋፈል ላይ በተመሠረተ አስተዳደር ለማዋቀር መሞከር ልዩን ከማስፋትና አዳዲስ ችግሮችን ከመፈልፈል ውጭ ሁሉንም ዜጎች በእኩል ዓይን የሚያይና ከአድሎዓዊነት የፀዳ፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሰፍን ለማድረግም ሆነ የኅብረተሰቡን ትሥሥር ለማጎልበት፣ አንድነቱን ለማጠናከርና በአጠቃላይም በአንድ አገር ዜጎች መኻል ሊኖር የሚገባውን ቅርርብና ትስስብ ለማስገኘት አይችልም:: ለምሳሌ ሳዳም ሁሴን የተባለን አምባ-ገነን ለማስወገድ በተወሰደው ጣልቃ-ገብ ጦርነት የኢራቅን ሕዝብ ግልፅ በሆነ መልክ በከርድ፣ በሺያና በሱኒ ከሦስት በመክፈል "አዲስ ኢራቅን" ለመፍጠር የተደረገው ጫና-አዘል ጥረት ኢራቅን ለእንዴት ዓይነት ኋላ-ቀር ኃይሎች እንደዳደጋትና የኢራቅን ሕዝብ በምን ዓይነት አስከፊ ማዕበል ውስጥ እንድትናጥ እንዳደረጋት እያየን ነው:: በእርግጥ የሳዳም ሁሴን አገዛዝ በሺያና ኩርዶች የአገሪቱ ዜጎች ላይ የተለዬ ጫና ያደርግና ግፍ ይፈፅም እንደነበር ይነገራል:: ሆኖም ግን ለሳዳም ሁሴን አገዛዝ ያልተመቹ ወይንም አሜን ብለው ያልተቀበሉ ሱኒዎች የዚያ አምባ-ገነን ግፍ ሰለባ አልነበሩም ማለት አይደለም:: ስለሆነም እያንዳንዱ የኢራቅ ዜጋ በኢራቃዊነቱ ለሁሉም የአገሪቱ ዜጎች እኩልነትና አርነት መቆም ሲኖርበት ከሌላው ኢራቃዊ ወገኑ ተለይቶ ብሔረሰብን/ጎሣን መሠረት ባደረገ ሁኔታ "የየራሱን" ጉዳይ እንዲፈታ በሚል መከፋፈልና የሰው ልጅ ሥልጣኔ ምንጭ ከሆኑት ቀደምት አገሮች አንዷ የሆነችውን አገር በሕዝብ ልዩነት ላይ በተመሠረተ አስተዳደር ማዋቀሩ የኢራቅ ሕዝብ እንደ አንድ አገር ሕዝብ ሣይሆን የተለያዩ መታወቂያዎችን ይዞ እንዲያድግና "የቅርብ ባዕድ" ሆኖ አንዱ ከሌላው በጎሪጥና በጥርጣሬ እየተያየ እንዲኖር ማድረጉ ለኢራቅ ሕዝብም ሆነ ለአካባቢው ዘለቄታዊ ሰላምም ሆነ መረጋጋት አዎንታዊ አስተዋጽዖ ሊኖረው ሲችል አይታየኝም:: ይኸ አንድን አገር በትኖ የመግጠም ወይም ቀዶ የመስፋት ጥረት በዜጎች ላይ ምን ያኸል ሥነ-ልቦናዊና አካላዊ ችግር እንዳስከተለ እየታየ ነው:: በዚኸ መልክ የተፈፀመው ኢራቃውያንን በጎሣ የመከፋፈል ድርጊትም ሕዝቡ እንደ አንድ አገር ዜጋ ሣይሆን ነህ ተብሎ በየተከተረበት "ክልል" ሆኖ እንዲያተኩርና መከፋፈሉን ተከትሎ በመጣ ቀውስ ውስጥ እንዲታመስ ስላደረገው እንደ አንድ አገር ሕዝብ በኢ-ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ላይ ዘምተው ሁሉም ዜጎች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ፍትኃዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በመገንባቱ ጥረት ላይ ምን ያኸል እክል እንደፈጠረባቸው ይታወቃል:: ሁኔታውም አንዱ በሌላው ላይ ያለው ጥርጣሬ እየጠነከረና አለመተማመን እየሰፋ እንዲሄድ ስላደረገ አገር-አቀፍ ምርጫ ተደርጎ እንኳን ማዕከላዊ መንግሥት ለመመሥረት ያጋጠማቸውን ፖለቲካዊ ጎሠኛነትን የተከተለ መሳሳብና እክል እያየን ነው::*

የፖለቲካዊ ብሔረሰበኘነት (የጎሣ ፖለቲካ) አንዱ መሠረታዊ ችግር በዚኽ ርዕዮት የሚመራ ድርጅት በታሪክ አጋጣሚ ለአገራዊ ሥልጣን መብቃት ቢችልም እንኳ አገር-አቀፍ ሕጋዊ ተቀባይነትም ሆነ ተዓማኒነት ለማግኘት እንደማይችል ነው:: ምንም እንኳ ያለ ሕጋዊና ሰላማዊ መንገድ እንዲሁም ያለ ዜጎች ይሁንታና ነፃ ፈቃድ ሥልጣን ላይ የሚወጣ ማንኛውም ክፍል በሁሉም ቀርቶ በአብዛኛው የአገሪቱ ዜጎች ዘንድ ሙሉ ተቀባይነትና አመኔታን ማግኘት የሚሣነው ቢሆንም፣ በተለይ ለተወሰነ የአገሪቱ ክፍል ብቻ የቆመ ሲሆን ደግሞ አገር-አቀፍ አመኔታንና ተቀባይነትን ማግኘት በጣሙን እንደሚሳነው የታወቀ ነው:: ለተወሰነ የአገሪቱ ክፍል ብቻ የቆመ ድርጅት ለሥልጣን በሚበቃበት ጊዜ የመንግሥታዊ መዋቅሮችን ዋና ዋና ቦታዎች ዓይን ባወጣ ይሉኝታ-ቢስነት የሚይዙትና የሚቆጣጠሩትም የዚኹ ድርጅት አባላት ስለሚሆኑ አጠቃላይ ሕዝቡ (በተለይም ድርጅቱ እወክለዋለሁ ከሚለው ብሔረሰብ ውጭ ያሉት) እና ለሥልጣን በበቃው የብሔረሰብ (ፖለቲካዊ ጎሠኛ/ጎጠኛ) መኻከል ግልፅ የሆነ አለመተማመን መኖሩ ጉዳዩን ያባብሰዋል:: ይኽ ሂደት በቀጠለ ቁጥርም በገዥው ክፍል በኩል ሥልጣን ላይ መቆየት ብቸኛው የመኖሪያና የደኅንነት ዋስትና ተደርጎ ስለሚወሰድ በቀጣይነት አምባ-ገነን ከመሆን አይዘልም:: በመሆኑም የሚቃወመውን ሁሉ በተገቢ ተቀናቃኝነት ሣይሆን በጠላትነት ፈርጆ ሕዝብን በዘፈቀደ ማተራመሱ አይቀሬ እውነታ ይሆናል:: ከዚኽ አንፃርም ለተወሰኑ የአገሪቱ ክፍል ብቻ ቆሜያለሁ የሚሉ ድርጅቶችን የሚመሩ ግለሰቦች የሁሉንም የአገሪቱ ዜጎች ይሁንታ፣ አመኔታና ከበሬታ ማትረፍ እንደሚገዳቸው ሁሉ በአንፃሩ እነዚኽ ወገኖች አገርን ለማስተዳደር ብቃቱና ችሎታው ሊኖራቸው ሲችል እራሣቸውን "የኔ" ነው በሚሉት ጎሣ/ብሔረሰብ ፖለቲካ ውስጥ በማቀባቸው ጠቅላላው የአገሪቱ ሕዝብ ከነሱ ሊያገኝ የሚችለውን አመራር እንደነፈጉት ሊታወቅ ይገባል፣ ያሣዝናልም:: ግን ምጫቸው ነውና ምንም ማድረግ አይቻልም:: ለምሣሌ አፄ ካሌብ ትግሬ ነኝ፣ ቴዎድሮስ አማራ ነኝ ፣ በካፋ ኦሮሞ ነኝ፣ ኢሌኒ ሃድያ ነኝ፣ ዮሐንስ ትግሬ ነኝ፣ ሐመልማል ከምባታ ነኝ፣  ወዘተ.. ቢሉ ኖሮና ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ የየጎጣቸውን ጥቅም ለማስከበር ለየጎሣቸው ብቻ የቆሙ ቢሆኑ ኖሮ አገር-አቀፍ ከበሬታን፣ አመኔታም ሆነ ተቀባይነትን ማግኘት ባልቻሉም ነበር:: ሕዝቡም እነዚኽንና ሌሎች መሪዎችን በጉድለቶቻቸው ወይም በአገዛዛቸው ዴሞክራሲያዊ አለመሆን ወይም በልዩ አድራጎቶቻቸው ሊነቅፉቸውም ሆነ ሊጠላቸው የሚችል የኅብረተሰብ ክፍል ሊኖር ቢችልም እንኳ ያ ስሜት ግልፅ የሆነ ጎሣዊ መልክ የሚይዝበት ሁኔታ አልታየም:: ምክንያቱም መሪዎቹ ጠቅላላውን የአገሪቱን ሕዝብ "ሕዝቤ" ብለውና ሁሉንም የነሱ ወገን አድርገው ነበር የሚያዩት:: ሲበድሉትም ታጊያ እንዲሁ!

በሕወሓት ዙሪያ የተፈጠሩና በኢሕአዴግ ስም እንዲሰባሰቡ የተደረጉ ድርጅቶች ከፈጠራቸው ድርጅት ከሕወሓት የተለየ የፖለቲካ ፍልሥፍናና የአደረጃጀት ዘይቤ እንደሌላቸው ይታወቃል:: ስለሆነም የኢሕአዴግ "አውራ" ድርጅት ሕወሓት በሁሉም ስም የፈለገውን ለማድረግና መርኃ-እቅዶችን በማዕከል ለመተለምም ይሁን እነኛን እቅዶች በተግባር ለመተርጎም የውስጥ እክል የለበትም:: በአንፃሩ ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ቁጥሩ በየጊዜው እየጨመረ የመጣው ለለውጥ የቆመው ክፍል አንድ-ወጥ እንዳልሆነ ግልጥ ነው:: ይኽ ክፍል በአመለካከት፣ በፖለቲካ ፍልሥፍና፣ በዓላማ፣ በግብ፣ በአደረጃጀት፣ በትግል ስልትና ትልም ልዩነቶች ያሏቸው ድርጅቶችን ያቀፈ ነው:: ይኽ በአገዛዙና ለለውጥ በቆመው ክፍል ያለው አንደኛ መሠረታዊ ልዩነት ነው:: የኢሕአዴግ ዓይነት አደረጃጀት ለ"አውራው" ድርጅት ለሕወሓት መረን የለቀቀ የሥልጣን ክምችትና በዚያም አማካይነት ፍጹም አምባ-ገነን የመሆን አውላላ ዕድልን የሚከፍት ስለሆነ የተለዩ አስተሳሰቦችን ለመቀበል ቀርቶ ለማስተናገድ እንኳ ስለማይቻለው ለመድብለ-ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን ከፍተኛ ጠር ይሆናል:: የፖለቲካ ስሊቶች ሁሉ ያ ተግበስብሶ የተያዘ ሥልጣን እንዳይሸራረፍ በቀናዒነት ከመጠበቅ አኳያ ብቻ ስለሚሆኑ፣ ገዥው ክፍል "ተቃዋሚ" የሚባለውን የሚያየው ይኽ ክፍል ለሕዝብ ከሚያቀርበው አማራጭ አንፃር ሣይሆን ከሱ ሥልጣን ማጣት ማዕዘን ብቻ ስለሆነ በአገራዊ አማራጭነት ሳይሆን በጠላትነት ይሆናል ማለት ነው::

ለለውጥ የቆመው ክፍል በርካታ ችግሮች እንዳሉበት ግልፅ ነው:: ወጥ አመለካከትና አደረጃጀት እንደሌለው ሁሉ የሚያደርገው ትግል ይኽንኑ የአቋምና የአደረጃጀት ጠገግ የተከተለ ፈርጀ-ብዙ መሆኑ አይቀሬ ነው:: ሆኖም ከላይ ሲታይ ከሞላ-ጎደል ሁሉም በሚያሰኝ መልክ በቅርብ-ጊዜ-ግቡ ማለትም የኢሕአዴግ ይዞታ መለወጥ ላይ ስምምነት አለ ማለት ይቻላል:: 'ከላይ ሲታይ' ያልኩበት ምክንያት በኢሕአዴግ ይዞታ መቀየር ላይ ስምምነት ሊኖር ቢችልም እያንዳንዱን በለውጥ ኃይሉ ውስጥ ያለ ድርጅት ወደዚያ አቋም ያደረሰው ልዩ ምክንያትም ሆነ የኢሕአዴግ መለወጥ እንዲያስገኝ በሚፈለገው ግብ ላይ ተመሣሣይ አቋም አለ ማለት ስለማይቻል ነው:: እንግዲህ ይኽንን መሠረታዊ የአመለካከትና የግብ ዝንፈት ይዞ ነው በልዩነት ለመሰባሰብና በአገሪቱ ላይ ያለውን

ሁኔታ ለመቀየር ጥረት ሲያደርግ የቆየውና አሁንም ጥረት የሚያደርገው፡፡ ይኸንን አውቆ ግን ከወዲሁ መላ ማበጀት፣ ማለት የአስተሳሰብ መሸጋሸግ እንዲኖር ማድረግ ወይም በየአስተሳሰቡና በልዕለ-ግቡ ዙሪያ ባለ አስተሳሰብ ላይ የተመረኮዘ አዲስ አደረጃጀትን መያዝ አማራጭ ላይኖረው ይችላል፡፡ በአዘቦታዊ የትግል ሂደት እስካሁን እንደተደረገው ይኸን ተቃርኖና የሰረፀ ልዩነት በውስጡ ይዞ በጊዚያዊነት አብሮ ማዝገም ይቻላል፡፡ እንዲያውም ለውጥም ሊያስገኝ ይችላል፡፡ ነገር ግን አሁን ያለው የአገሪቱ ሁኔታና እንዲለወጥ የሚፈለገው ኃይል በዚኸ ተለምዷዊ አሠላለፍ አገርንና ሕዝብን በሚጠቅም መንገድ ሊለወጡ የሚችሉበት አንዳች ሥነ-ምክንያት አይኖርም፡፡

እርግጥ ነው በአገሪቱ የሚገኙ ዜጎች ጥያቄዎቻቸውንና ብሶቶቻቸውን የሚያሰሙባቸውና የሚገልጹባቸው መንገዶች የግድ አንድ ዓይነት እንዲሆኑ አይጠበቅም፡፡ ብሶቶችን ተመርኩዞ የሚቀርቡ ጥያቄዎች በአግባቡ ካልተመለሱ ወይም ለማስተናገድ የሚያስችል ሁኔታ ከሌለ ልዩ ልዩ መልኮች እንደሚይዙና በተለያዩ መንገዶች እንደሚገለጹ ሁኔታው የግድ እንደሚልም የታወቀ ነው፡፡ በተለይም አሁን በአገራችን እንደሚታየው የፖለቲካ ምኅዳሩ ጨርሶ እየከሰመ በመሄዱ ምክንያት ብሶቶችን በሰላም ማስተናገድ ስለማያስችል አገራችንን ወዳልተፈለገና ሁሉንም ጎጂ ወደ ሆነ አቅጣጫ እንደሚወስድ ደግሞ ግልፅ ነው፡፡

በኔ አመለካከት ለጋራ ትግሉ አለመሣካት አንደኛው ዋና እክል መሰባሰቡ እዚኸ ያልተጣጣመ እይታ ላይ ስለሚመሠረት ነው፡፡ በአንዳንድ ወገኖች "የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጭው" እንዲሉ ዓይነት "ወያኔ/ኢሕአዴግን ለማስወገድ (ለመጣል) ማንም ምንም አቋም ይኑረው ምን፣ ወያኔን እስከጠላ ድረስ አብሮ መሰለፍ ይቻላል" የሚል አመለካከትና ግፊት እንዳለ ይታወቃል፡፡ ለዚኸም አንዳንድ ከአገራችን ሁኔታዎች ጋር ጨርሶ ያልተዛመዱ የሌሎች አገሮችን "የተሳኩ" ጥረቶች፣ ለምሳሌ እንደ እንግሊዙ የ1688-89 'ታዋቂ (ዝነኛው) አብዮት' (Glorious Revolution) የመሣሰሉት በዋቢነት ሲጠቀሱም ተስተውሏል፡፡ በጥሞና ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ግን ከዚኸ ሁሉንም የማካተት በጎ ፍላጎት ተገፍተን የምናቋቁመው "ግንባር፣ ኅብረት፣ ጥምረት፣ ወዘተ.." እስከዛሬ ከተደረጉት የጋራ ትግል ጥረቶች የተለየ ምን ማድረግ እንደሚቻል ነው፡፡ የማሲንቆ ተጫዋቹና የውሃው ሙላት ታሪክ ካልሆነ በስተቀር እንደሚታወቀው ባለፉት አሥራ-ዘጠኝ ዓመታት በተደረጉ የጋራ ትግል ጥረቶች "ማንንም ሳያገልሉ" ለመሰባሰብ ነበርኮ የተሞከረው፡፡ ስለሆነም ወደ-ፊት ለመገሥገስ ከመሞከሩ በፊት ቀደም-ሲል የተደረጉ የጋራ ትግል ጥረቶች ለምን የታሰበውን ያኸል ውጤት እንዳላስገኙ በቅርበት መመርመሩ ለወደፊቱ ትልም መሣካት እጅግ ጠቃሚ ትምሕርቶችን ስለሚሰጥ ቅድሚያ ሊሰጠውና ሊተኮርበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ይኸን ደግሞ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ አሁን ማድረጉ አስፈላጊ የሚሆነው በተለይ ድኅረ-ምርጫ-ሁለት-ሽህ-ሁለት ያለው የአገራችን ሁኔታ የችግሮቻችንን መሠረት የሚያጠናክርና ሕዝባችንንም ለአጠቃላይ ተስፋ-መቁረጥ የመዳረግ ዕድሉ ሰፊ ስለሆነና ለለውጥ የቆመው ኃይልም ችግሮቻችንን የማይቀርፉና አልፎም ሊያባብሱ የሚችሉ የተቻኮሉ እርምጃዎችን እንዲወስድ በር ስለሚከፍት ነው፡፡

ዞሮ ዞሮ ለለውጥ የቆመው ኃይል ለኢሕአዴግ አሣልፎ የሰጠውን ቅድሚያ መልሶ ካልወሰደና ከቅጥ-ያጣ ተከላካይነት እስካልወጣ ድረስ ምንም ያኸል መስዋዕትነት ቢከፈል ትግሉ ውጤት ያመጣል ብሎ መጠበቅ አይቻልም፡፡ ወቅቱ ደግሞ አስቸጋሪ ሊሆን የመቻሉን ያኸል ለለውጥ የቆመው አገር-ወዳድና ሕዝባዊ (ዴሞክራት) ኃይሉ ለሚያደረገው ትግል መሰል-የሌለው መልካም አጋጣሚን የፈጠረ ሁኔታ እንደሆነም ያጤኗል፡፡ ሁኔታው ግን ቆሞ ስለማይጠብቅ በአዲስ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ቁርጠኛ አሰላለፍ በመያዝ ፈጣን ግን በደንብ የታሰበበት ምላሽን ይጠይቃል፡፡

ለለውጥ የቆመው አገር-ወዳድና ሕዝባዊ (ዴሞክራት) ኃይል በሚያደርገው የጋራ ትግል ጥረቱ የሚከፍለውን መስዋዕትነት የሚመጥን፣ የሕዝቡን ስሜት የሚማርክም ሆነ ሙሉ አመኔታን ሊያሳድር የሚችል ውጤት ማስመዝገብ ካልቻለባቸው ዓበይት ምክንያቶች ውስጥ መሠረታዊ የአስተሳሰብ፣ የአደረጃጀት፣ የስልትና ስትራተጂ ችግሮች ዋነኞች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡
እያንዳንዳቸውን ከማየታችን በፊት ከተደረጉ የጋራ ትግል ጥረቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹን ማየቱ ስለሚጠቅም ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ) ጀምሮ በተለይ ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ወዲኸ የተፈጠሩትን ዋና ዋና የድርጅቶች የጋራ መታገያ መድረኮች በአጭር በአጭሩ እናያለን፡፡

*በክፍል አራት ይቀጥላል.........*